PANORAMA # 7

# የትዝብት አድማስ

## ታህሳሥ 24 2000 ዓም

## የዘመናት መለዋወጥ

*በዓለም ያሉ ሀገራት የአዲስ ዘመን አለዋወጥ በዓላቸውን፥ እንደ ዕምነታችው፥ ባኅላቸው፥ ታሪካቸውና አምልኮታቸው ያከብሩታል። አከባበር ከተባለም የኛውም እንደዚሁ ነው። አሮጌው እያለፈ በአዲስ መተካት የተፈጥሮ ህግም በመሆኑ፥ አሮጌውን እየሸኙ አዲሱን መቀበል የነበረ ፥ ያለና ወደፊትም የሚቀጥል ለመሆኑ ሁሉም ያምንበታል። ያለፈውን መልካምም ሆነ መጥፎ ትዝታ በአዲሱ ተስፋና ራዕይ፥ መልካም ምኞትና ብሩኅ ጉጉት ለመተካት ይሻሉ። "የኅመን ምቸት ውጣ፥ የስጋ ወጭት" ግባ ይባላል። "ያለፈውን መከራ በአዲስ ደስታ ለውጥልን" እያለ የተስፋ እንጉርጉሮ ማሰማት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያልተለመደ አይደለም። የሀገሩ ዘመን ኅልውና መቆጠር ከተጀመረ አንስቶ፥ ኑሮው ያልተሻለለት መሆኑን ስለሚያውቅ፥ ዘመን ሄዶ ዘመን በተተካ ቁጥር የተሻለ ህይወት አገኛለሁ ብለው ከሚጓጉ የዓለም ሕዝቦች መካከል ኢትዮጵያዊ ዜጋ የመጀመሪያውን ቦታ ይዟል። የተስፋ ዳቦ እየገመጡ መኖር፥ "ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ" እያሉ ማቆዘም፥ የህይወታችን ዘየ ካደረግነው ዓመታት አስቆጥረናል። ለእኛ ለኢትዮጵያውን፥ በተለይም ደግሞ በገጠር ለሚኖሩት በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ደሃ ገበሬዎች፥ የዘመናት መለዋወጥ ምንም የሚያመጣው የተሻለ ነገር አይኖርም። ኑሯችን ሁሉ ቋቱ ጠብ የማይል "እየፈጩ ጥሬ" ሆኖብናል።*

*በተስፋና ራዕይ መኖር የህይወት ዋስትና ይሆናል ባይባልም፥ ተስፋን አንግቦ በተግባር ላይ ማተኮር ግን ተጨባጭ ውጤት ለማስመዝገብ ይረዳል። ተስፋ ያደረግነውን ጉዳይ፥ በተጨባጭ ለመተርጎም የሚያስችል ሥርዓት ባለማግኘታችን፥ ዝንተ-ዓለማችን ከድኅነት፥ ከረሀብና ከበሽታ ለመላቀቅ አልቻልንም። በኢትዮጵያ ሀገራችን አምባገነኖች ብቻ ሳይሆኑ ኅብረተሰቡም ከችግሩ ጥንካሬና ክብደት ለመላቀቅ ሲል፥ እራሱን በተሰፋ እያታለለ ይኖራል። አንድ ኮሶ የተጣባው ሰው ተውሳኩን ለማስወገድ፥ የኮሶ መድኅኒት ሲጠጣ፥ የኮሶው መራራነት እንዳያንገፈግፈው፥ ቤተሰቦቹ፥ " ዶሮ ማታ! ዶሮ ማታ!" እያሉ ያጽናኑታል ይገፋፉታል። ኮሶውን በድፍረት እንዲጠጣ! ልክ ኮሶውን ጭልጥ አድርጎ ከጠጣ በኋላ፥ ወዲያውኑ " እንኳን ዶሮ የለም ሽሮ" በማለት ማታ የዶሮ ወጥ እንደማይጠብቀው ዕቅጩን ይነግሩታል። ይህ አጭር ባኅላዊ ትዝብት፥ ሕዝባችን፥ በሥነ ልቦና ብቻ እየተፅናና የሚኖር መሆኑን ያመለክታል። ራስን እያታለሉ የመኖር ችሎታችን የቱን ያህል ሊጠቅመን እንደሚችል ማወቅ ግን አንችልም።*

በአብዛኛው የዓለም ክፍል ያሉ ሕዝቦች ያዲሱን ዓመት መለወጫ የሚያከብሩት፥ ለሚቀጥሉት ዓመታት የሚሰሩትን ብሄራዊ የልማት እንቅስቃሴና የዕድገታቸውን ዕቅድ በማውጣት ነው። በአዲሱ ዓመት፥ ስንት የትምህርት ፥ የሆስፒታል፥ የንግድና የእርሻ ተቋማት፥ የሳይንስና የቴክኒዮሎጂ ማዕከል፥ የውሃ መስኖዎች፥ የኃይል ማመንጫና እንዱስትሪዎች፥ የጤና አገልግሎቶች፥ የመገናኛና የመጓጓዣ አውታሮችን በማቋቋምና በመዘርጋት ላይ ነው። ይህ ሁሉ ሲደመር፥ ጠቅላላ የሀገራቸውን ዜጎች ሕይወት ወደተሻለ የኑሮ ደረጃ ለማሳደግ የሚደረግ ዕቅድና ብሎም ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚያስችል ብሔራዊ ፕላናቸው ወይም ዕቅዳቸው ነው። ባለፈው ዓመት የተገኘውን የልማትና ዕድገት ውጤት፥ ወይም ደግሞ፥ በዕቅዱ መሠረት ውጤት ሊያመጣ ያለተቻለበትን ሁኔታ እስከ ምክንያቱ፥ ለመገምገምና ብሎም ለወደፊቱ ዕቅድ ሲወጣ፥ ያ ችግር እንዳይደገም የሚታሰስበት፥ የድክመቶቹ ሰበቦች የሚመረመሩበትና ከአዲሱ ዓመት የልማት ዕቅዶች ጋር የሚነፃፀሩበት ወቅት ይሆናል።

አብዛኛዎቹ የዓለም ሕዝቦች አሁን ከደረሱበት የኑሮ ደረጃ ሊደርሱ የበቁት፥ በዕቅድና ዕቅዱንም ወደ ተጨባጭ ውጤት ለማስመዝገብ ተግቶ በመሥራት ብቻ ነው። ሌላ አብነት የላቸውም። ሁሉም ዜጋ፥ ዕቅድ አውጭው በሚያወጣለት ብሔራዊ ፕላን መሠረት ለዕድገት ከተባበረ፥ የተሳካ ውጤት የማያስመዘግብበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም። ታዲያ፥ ዜጎች በሙሉ ልብና መንፈስ ለሀገር ዕድገት ሊረባረቡ የሚችሉት፥ ከአንድ መሠረት ላይ ሲነሱ ነው። ይኸውም" የዴሞክራሲ ሥርዓትና የነፃነት መብት ተጎናጽፈው ሲገኙ ይሆናል። ይህ መሠረታዊ ጉዳይ ከሌለ፥ ሌላው ሁሉ ይሳካል ለማለት የሚቻል አይሆንም። ሰዎች በነፃነትና በራሳቸው አነሳሽነት ለመሥራት ዕድሉን ካገኙ ደግሞ ታአምር ለመስራት የማይጠበቅ አይሆንም።

አዲስ የልማትና የዕድገት ዕቅድ ሲወጣ፥ ነባሩን ለማሻሻል፥ ለማስተካከል፥ ብሎም ከዚያ ተነስቶ ለመቀጠልና ለማሳደግ እንጅ፥ ነባሩን እያጠፉና እያወደሙ አይደለም። የቆዩት ሰዎች የገነቡትን በማፍረስና በማጥፋት ሀ ብሎ መጀመር ምናልባት ከጥቅሙ ጎዳቱ የሚያዘነብል ይሆናል። ምዕራቡ ዓለም አሁን ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ ሊደርስ የቻለው፥ የቀደመው ትውልድ በገነባው ላይ ተነስቶ በመቀጠልና በማሳደግ እንጅ፥ የነበረውን እንዳልነበረ እያደረገ ድምጥማጡን በማጥፋት አይደለም። ይህ ክስተት ግን በእኛ ሀገር የተለመደ ተመክሮ አይደለም። አዲስ የሚመጣው መንግሥት ሁሉ የመጀመሪያው ዕቅዱ፥ የነበረውን በማጥፋት ላይ ይሆናል። ከዛሬ መቶ ዓመት በፊት በስንት ድካም ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ የተዘረጋችው አንስተኛና ብቸኛ የሆነቸው የባቡር ሀዲድ፥ ከመጨረሻዋ መስመር ፈቅ ሳትል፥እንሆ እስካሁን እዚያው አለች። ይባስ ተብሎ ዛሬ ጭራሽ የሚጠግናት በመጥፋቱ በመንኮታኮት ላይ ትገኛለች። አገልግሎቷም ከቀን ወደ ቀን እየተበላሸ በመሄድ ላይ ነው።

*ይህ የነበረውን በማውደም ፌሊጥ ላይ የሚመሰረተው አዲስ መጭ መንግሥት፥ የተካውን መንግሥት የጎዳው እየመሰለው፥ ብሔራዊ ተቋማትንና የልማት አውታሮችን ያወድማል ፡፡ ሀገርንና ሕዝብን የሚጎዳ ውድመት እያደረገ ታላቅ ብሄራዊ ወንጀል መፈጸሙን ግን ከቶ አይረዳውም፡፡ ሊረዳው ይችላል ተብሎ ቢገመትም እንኳ፥ ደንታ ይሰጠዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ይህ ድርጊት ለምን ወያኔ ይፈጽመዋል ተብሎም ሊጠይቅ የሚገባው አይመስለንም፡፡ ሊያስገርምም አይችልም፡፡ ምክንያቱም ወያኔ ከጥንት ከጧቱ ኢትዮጵያን ለማጥፋት የተነሳ ብሄረተኛ ድርጅት በመሆኑ ነው፡፡ ይህማ ባይሆን ኖሮ፥ የሀገሪቱን ታላላቅ ተቋማት ባላፈራረሳቸውም ነበር፡፡ ከሁሉም የሚያሳዝነው፥ ምናልባትም በሦስተኛው ዓለም ካሉት ሀገሮች ውስጥ ተወዳዳሪ አይገኝለትም የሚባለውን፥ የሀረር ጦር አካዳሚ ፍርስርሱን አውጥቶ፥ እንዳልነበረ ማድረጉ ነው፡፡ ይህንን የሚፈጽም ከይሲ ቡድን፥ ኢትዮጵያዊ መንግሥት ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ የውጭ ጠላትም እንኳ ቢሆን፥ ለራሱ ጥቅም ይገለገልበታል እንጅ ተቋማትን ከቶ አያፈርስም፡፡ ቀደም ሲል የአመረቃ ውጤት በማስመዝገብ የሚታወቀውን የወባ ማጥፊያ አገልግሎት ተቋም፥ ለምን ማጥፋት እንዳስፈለገው ምክንያቱን ለመረዳት ጤናማ አዕምሮ ላለው ሰው ይቸግራል፡፡*

*በዚህ በያዝነው ሳምንት ላይ ምዕራባውያን የአዲስ ዓመት መባቻ በዓላቸውን አክብረዋል፡፡ ሀገሮቻቸው በሰላም፥ በመረጋጋትና በብልፅግና እንዲቀጥሉላቸው የመልካም ምኞት መግለጫ ሲለዋወጡም ሰምተናል፡፡ ለበለጠ ዕድገትና ብልፅግናም የተቻላቸውን ሁሉ ጥረት እንደሚያደርጉ፥ በሚያወጡት የአጭርና የረዥም ጊዜ ዕቅድ ታዝበናል፡፡ እኛም ለሀገሮቻቸው ዜጎች መልካሙን ሁሉ ከመመኘት አንታበይም፡፡ ይህንንም የምንለው፥ ለማነኛው ሕዝብ ሁሉ መልካም ምኞትን መግለፅ፥ የማነኛው ሰብዓዊ ፍጡር መሠረታዊ ባኅርዩ በመሆኑ ብቻ ነው፡፡ መልካም ምኞትን ከመግለፅ ባሻገር ግን ስለ ሌሎች የዓለም ሕዝቦች ሰቆቃና ችግር ማንሳት ሚዛናዊ ይመስለናል፡፡*

*ምዕራባውያን አዲሱን የዘመን መለወጫ በዓላቸውን በደስታ ሲያሳልፉ፥ በርካታው የዓለም ሕዝብ ደግሞ፥ ሠላምና መረጋጋት በማጣት፥ በጦርነትና በዕልቂት ላይ ይገኛል፡፡ በተለይ ይህ ክስተት ጎልቶ የሚታየው በመልማት ላይ ያሉና ወደኋላ ቀርተዋል በሚባሉት ሦስተኛው ዓለም በሚኖሩ ሕዝቦች ላይ ነው፡፡ በሩቅና በመካከለኛው ምሥራቅ የሚኖሩ ሕዝቦች ለነፃነታቸውና ከውጭ ጣለቃ ገብነት ለመከላከል ሲባል የብዙ ሰላማዊ ሕዝቦችን ሕይወት የሚያጠፋ ዕልቂት እየተደረገ ነው፡፡ በተለይ ዛሬ ፥ በአብዛኛው የአፍሪካ ሀገሮች የሰው ዘር እስከ ማጥፋት የሚደርስ አሰቃቂ ጦርነት በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በኡጋዴን፥ ኢትዮጵያ፥ በሞቃዲሾ ሶማሊያ ፥ ዳርፉር ሱዳን፥ በኮንጎ ሪፑብሊክ፥ የሚካሄደው የሰው ልጅ ዕልቂት፥ የምዕራቡ ዓለም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚያካሂደው ነው፡፡ ይህንን ዕልቂት ለማቆም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም ይሁን የአፍሪካ ኅብረት የሚያደርጉት ጥረት ፥ከከንፈር መምጠጥ ያለፈ ሀዘኔታ ሊሆን አልቻለም፡፡ በሁለቱ አምባገነን ድርጅቶች፥ ማለት፥ በሻዕቢያና በወያኔ መካከል የሚደረገው የጦርነት መሰናዶ፥ ወደ ውጊያ*

ከተለወጠ የሚያመጣውን አሰቃቂ ዕልቂት መገመት አያስቸግርም። ምዕራብያኑ፥ "ዕሳትና ገለባ ያድርጋችሁ" ከማለት አልፈው፥ ጭፍሮቻቸውን ጦርነት አታድርጉ በለው ይቆጧቸዋል ተብሎ አይጠበቅም። ይህ በሦስተኛው ዓለም በሚኖሩ ሕዝቦች ላይ የሚደረገው ዕልቂትና በደል እየተከናወነ ያለው፥ ምዕራብውያኑ አዲሱን የዘመን መለዎጫ በዓላቸውን እያከበሩ፥ ደስታቸውንም የሚገልፁበትን ርችት በሚተኩሱበት ወቅት ነው። ይህንን መጥቀሳችን እንዲያው ለንፅፅር ግንዛቤ ብለን እንጅ፥ የእኛን ችግር ባዕዳን ሊፈቱልን ይችላሉ ከሚል ከንቱ ምኞት አይደለም።

በእኛ ዕምነት፥ የሀገራችንን የደለበ ችግር መፍታት የምንችለው በዋናነት እኛው ራሳችን ብቻ እንደሆነ ደጋግመን ደጋግመን የምንገልፀው ጉዳይ ነው። ይህንን ስንል የሚከተሉትን ዓበይት ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ ነው።

በቅድሚያ የችግራችንን መሠረታዊ መንስዔዎች ለይተን ማወቅ ይኖርብናል።

- ዋናው ችግራችን፥ የችግራችንን መሠረታዊው ችግር፥ አለመረዳታችን ነው ተብሎ ይታመናል። መሠረታዊ ችግሮቻችንን በሚገባና በቅድሚያ ሳናውቅ፥ ያላወቅነውን ችግር ለመፍታት ስንል ወደመፍትሄ ፍለጋ ስንባዝን ዓመታት አስቆጥረናል። ታዲያ የችግሩ መንስዔው እኛው ራሳችን ነን ወደ ሚለው ድምዳሜ መሄድ ከቻልን፥ እኛው እራሳችን የሀገራችን ችግር ፈጣሪዎች ከመሆን መዳን አለብን ማለት ነው።
- የችግራችን መንስዔው እኛው ራሳችን ነን ሲባል፥ ወያኔን ተፃርርው የቆሙት ፓርቲዎችና ድርጅቶች ሊያስተባብራቸው ያልቻልውን ምክንያት ተረድተው፥ ችግሩንም አስወግደው ሊተባባሩ አለመቻለቻው ነው ለማለት ነው። ዘመንን እያስቆጠርን በዘመን ቆጠራ ከምንረባረብ፥ ዘመንን ተጠቅመን በዘመን ከሠራንበት ለችግራችን መፍትሄ እናገኝለታለን።
- ለአለፉት አስራ ሰባት ዓመታት የተቃዋሚ ድርጅቶችን ለማስተባበር የተደረጉት ጥረቶች ሁሉ እስካሁን ያመረቃ ውጤት አላስገኙም። አብዛኛዎቹ ጥረቶች ያደረጉት ሂደት ቢኖር ፥እየተቃቀፉ፥ መጠላለፍን፥ እየተጨባበጡ መቧቀስን፥ እየተሳሳሙ መነካከስን ብቻ ሆኖ ቀርቷል። ይህ ድርጊት ማንን እየጠቀመ ማንንስ እንደሚጎዳ መተንተን የሚያስፈልገን አይመስለንም።
- የኤንዶኔዥያ ሕዝብ አንድ ተረት አለው ይባላል። ይኸውም፥ "ማነኛውም ጊዜ፥ ማነኛውንም ችግር ይፈተዋል" የሚል ነው አሉ። አየ፥ እኛ ኢትዮጵያውያንስ፥ በዚህ ይትበኃል ልንስማማ ይገባናል ለማለት አንችገራለን። ምክንያቱም፥ በጊዜ ብዛትና ርዝመት ቢሆን ኖሮ፥ የኛ ችግር እስከሁን ድረስ ከኢትዮጵያ ምድረ- ገፅ ተጠራርጎ በወጣልን ነበር። ያ ግን አልሆነም።

**ታዲያ ምን ይሻላል? የተቃዋሚ ድርጅቶች በእርግጥ የቅድሚያ አጀንዳቸው ኢትዮጵያን ከጥፋት ማዳን ከሆነ÷ያላቸውን ልዩነት በአስቸኳይ አስወግደው÷ ወያኔን ከምንሊክ ግቢ ማስወጣት አለባቸው።**

**የዘመን መለዋወጥን እያከበሩ መኖር ብቻ ለሀገር ዕድገትም ሆነ ብልፅግና የሚያመጣው አንዳችም ፋይዳ አይኖርም። እኛ ግን ወያኔ ተንበርክኮ የኢትዮጵያ የብሩኅ ተስፋ ዘመን እስከሚመጣ ድረስ ትግላችንን አናቆምም።**